# ከውል ውጪ ያለ ሃላፊነት፤ የካሳ አወሳሰን እና አከፋፈል በአፋር ባህላዊ ህግ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ይድነቃቸው ከበደ
ኢሳያስ አየለ
ገ/መስቀል ገ/ዋህድ

## በጥናቱ የቀረበ ምክረ ሀሳብ

1. .በአሁኑ ሰአት የወረዳም ሆነ በአንዳንድ ከባድ ጉዳዮች የክልሉ መንግስት የባህላዊ ህግ ተቋም እና ሽማግሌዎች እንዲንቀሳቀሱ መፈቀዱ መቀጠል አለበት፡፡
2. .በባህላዊ ህግ መገልገል ራስን በራስ የማስተዳደር መብት መገለጫ ከመሆኑም ባሻገር የውስጥ ችግሩን በውስጥ ለመፍታት ለሚያደርገው ጥረት አበረታች በመሆኑ ሊጠናከር ይገባዋል፡፡
3. በክልሉም ሆነ በፌደራል ደረጃ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የሚወጡ ህጎች ነባሩን የህብረተሰብ ህጎች ከግምት ያስገቡ መሆን ይገባቸዋል
4. የባህላዊ ህጉ ስርአት በግጭት አፈታትም ሆነ በካሳ አከፋፈል ረገድ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ከመደበኛው ህግ የተሻለ በመሆኑ የሚኖረው ሚና መጎልበት ይኖርበታል፡
5. የክልሉ አቅም በተለይም በሰለጠነ የሰው ሓይል መጎልበት ይኖርበታል፡፡
6. በጥናቱ እንደተገኘው የአፋር የመድኣ ስርአት በተለይም ከውል ውጪ ሃላፊነትን እና የካሳ አከፋፈልን በተመለከተ በፌደራሉም ሆነ በክልሉ መንግስት የህግ አውጪም ሆነ አስፈጻሚ አካላት እውቅና ሊሰጠው ይገባል፡፡
7. የባህላዊ ህጉ እውቅና ተሰጥቶት ጉድለቶቹ ታርመህና ተስተካክለው መደበኛነት የሚተገበሩበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡
8. .በክልሉ ለሚኖሩ ነዋሪዎች መደበኛውና ባህላዊው የህግ ሥርዓት አብረው እንዴት መሄድ እንዳለባቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
9. መሰረተ ልማት የፍትህ ተደራሽነት በተሟላ ሁኔታ እንዲተገበር አስፈላጊ በመሆኑ መሠረተ ልማት በተገቢ መንገድ መሟላት ይኖርበታል፡፡
10. ባህላዊ ህጉ የሚታዩበትን የህግ ክፍተቶችን በማስወገድ የህግ ስርአቱ ቀጣይነቱን ጠብቆ እንዲሄድ መደረግ አለበት፡፡ በዚህ ረገድ የባህላዊ ህጉ የሚኖረው ሚና ሊጠናከር ይገባል፡፡
11. ባህላዊው የፍትሕ ሒደት ሴቶችን በእኩልነት የሚመለከትበትን ሁኔታ እንዲፈጠር የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ሊተገበሩ ይገባል፡፡
12. የባህላዊው ህግ ከነገሮችና ከጊዜዎች ጋር የመሻሻል፣ የመለዋወጥ ባህሪውን በመመርኮዝ ከወቅቱና አለም ከደረሰበት የእድገት ደረጃ ጋር ባህሉን የማሳደግ ጥረት ቢደረግ ጥሩ ነው፡፡
13. ለእንደዚህ አይነት ተመሳሳይ ጥናቶች ትኩረት በመስጠት በጥናቶቹ የሚገኙ ውጤቶችን እና አስተያየቶችን መቀበል ተቀብሎም ተግባራዊ ማድረግ ለአጠቃላይ የፍትህ ስርዓቱ መሻሻል ጠቀሜታ ይኖራቸዋል